## ቀደም ብሎ ካንሰርን (ነቀርሳ) ለማግኘት የሚደረጉ ምርመራዎች

አውስትራሊያ ሶስት የካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራሞች አሏት፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች የአንጀት፣ የጡት እና የማህፀን በር ካንሰር የመጀመሪያ ምልክቶችን ለማግኘት ቀላል ምርመራዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ካንሰርን ቀደም ብሎ ማግኘቱ ለማከም ቀላል ያደርገዋል፣ ብሎም በህይወት የመትረፍ እድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡

ምርመራው የካንሰር ምልክት ለሌላቸው ሰዎች ነው፡፡ የካንሰር ምልክቶች ከታዩ፣ ለሐኪምዎ ይንገሩ፡፡

አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ (ጊዜያዊ) የሜዲኬር ካርድ ካለዎት ሦስቱ ምርመራዎች ነፃ ናቸው፡፡ የሜዲኬር ካርድ ከሌለዎት ለምርመራዎቹ ምን ያህል እንደሚያስወጣ ለማወቅ ከሐኪምዎ ጋር ይነጋገሩ፡፡

### የካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ሕይወትዎን ሊያድን ይችላል፡፡

ስለ አንጀት፣ የጡት ወይም የማህፀን ጫፍ ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እነዚህን ይጎብኙ

- cancersa.org.au
- breastscreen.sa.gov.au
- ncsr.gov.au

ተመርምረው ካንሰር ከተገኘብዎት በኋላ ድጋፍ ከፈለጉ፣ **ለካንሰር ካውንስል ደቡብ አወስትራሊያ (SA)** በ **13 11 20** ይደውሉ፡፡



ይህ የመረጃ ምንጭ የተዘጋጀው በደቡብ አውስትራልያ የካንሰር ካውንስል/Cancer Council SA እና በደቡብ አውስትራልያ ብሬስትስክሪን/BreastScreen SA ሲሆን የሕትመት እና የትርጉም ሥራ በገንዘብ የተደገፈው በካንትሪ ኤሴ ፒኤችኤን/Country SA PHN ነው፡፡

Cancer Council SA

ስለ ካንሰር ነፃ* እና ሚስጥራዊ መረጃ እና ድጋፍ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 9.00 ሰኣት እስከ ምሽቱ 5.00 ሰኣት፡-

- ወደ ካንሰር ካውንስል በ**13 11 20** ይደውሉ
- በኦንላይን በ **cancersa.org.au** ቻት ያድርጉ
- ኢሜይል **askanurse@cancersa.org.au**

ነፃ* የትርጓሜ አገልግሎት በ **131 450** ይገኛል፡፡

*የአካባቢ የስልክ ጥሪ ዋጋ

በፌብርዋሪ 2025 ተገምግሟል

Amharic | አማርኛ

Cancer Council SA

# ቀደም ብሎ ካንሰርን (ነቀርሳ) ለማግኘት የሚደረጉ ምርመራዎች

## ስለ አውስትራሊያ የካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራሞች መረጃ



ካንሰርን አስቀድሞ ማወቅ

ለመረጃ እና ድጋፍ

**131120**

**cancersa.org.au**




# የአንጀት ካንሰርን ቀደም ብሎ ማግኘት

አውስትራሊያ ብሄራዊ የአንጀት ካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራም አላት። መርሃግብሩ የአንጀት ካንሰር የመጀመሪያ ምልክቶችን ለማግኘት ቀላል ምርመራን ይጠቀማል፤ ይህም ምልክቱ ለእርስዎ ከመታየቱ በፊት ነው። መመርመሪያው ወደ ቤትዎ በፖስታ ይላካል።

ዕድሜያቸው ከ45-74 የሆኑ ሁሉም አውስትራሊያውያን በየሁለት ዓመቱ የአንጀት ካንሰር ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

**ዕድሜ 45–49፦** የመጀመሪያውን የአንጀት ካንሰር መመርመሪያ በኦንላይን ይዘዙ። ከዚያ በኋላ በየሁለት ዓመቱ አዲስ መመርመሪያ በቀጥታ ያገኛሉ።

**ዕድሜ 50-74፦** ማዘዝ ሳያስፈልግ በየሁለት ዓመቱ የአንጀት ካንሰር መመርመሪያ ይላክልዎታል።

### የካንሰር ካውንስል ኤስኤ (SA) የሚከተለውን ይመክርዎታል፦

- የምርመራ እቃዎን/ ኪትዎን በፖስታ እንደደረስዎት ምርመራውን አጠናቀው መመለስ።
- የአንጀት ካንሰር ምልክቶች ካሉብዎ ሐኪምዎን ማየት። ምልክቶቹ ከፊንጢጣዎ ደም መፍሰስ፣ ከተጸዳዱ በኋላ በሽንት ቤት ወይም በሽንት ቤት ወረቀት ላይ ደም ማየት፣ ያልታወቀ የሆድ ድርቀት ወይም ተቅማጥ ወይም መነሻው ያልታወቀ ድካምን ያካትታሉ።
- በቤተሰብዎ የአንጀት ካንሰር ታሪክ ካለ ሐኪምዎን ያነጋግሩ።

**QR ኮዱን ስካን በማድረግ የሚከተለውን ያድርጉ፦**

- **የመጀመሪያውን የምርመራ እቃዎን/ ኪትዎን ወይም ምትክ መመርመሪያን ይዘዙ።**
- **በቋንቋዎ መረጃ ያግኙ።**



# የጡት ካንሰርን ቀደም ብሎ ማግኘት

ብሬስትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) የጡት ካንሰርን ቀደም ብሎ ለማግኘት ነፃ የማጣሪያ ማሞግራም ይሰጣል። ማሞግራም የጡት ኤክስሬይ ነው።

የማጣሪያ ማሞግራሞች እድሜያቸው 40 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች በተለይም ከ50-74 አመት ለሆኑ ሴቶች ነው።

ነፃ የማሞግራም ቀጠሮ ለማስያዝ የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ ወይም ለብሬስትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) በ 13 20 50 ይደውሉ። ያለ ምንም ወጪ ለቀጠሮዎ ሴት አስተርጓሚ ሊመድቡለዎት ይችላሉ።

ሁሉም ሰራተኞች ሴት ናቸው። ለመገኘት ከዶክተርዎ ሪፈራል አያስፈልግም።

### የካንሰር ካውንስል ኤስኤ እና ብሬስትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) የሚከተለውን ይመክራሉ፦


- በየሁለት አመቱ ነጻ የማጣሪያ ማሞግራም ማድረግ።
- ማናቸውንም ለውጦች እንዲያስተውሉ የጡትዎን መደበኛ መልክ እና ስሜት ማወቅ። ለውጦች እብጠት፣ የጡት ጫፍ ፍሳሽ ወይም ሌላ ለእርስዎ ያልተለመደ ለውጥ ያካትታሉ።
- ማንኛውንም ለውጦች ካዩ፣ የማጣሪያ ማሞግራም ለእርስዎ ተገቢ ስላልሆነ ሐኪምዎን ማየት።

**breastscreen.sa.gov.au ይጎብኙ፡**

- ስለ ማሞግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት።
- በቋንቋዎ መረጃ ለማግኘት።

**QR ኮዱን ስካን በማድረግ የሚከተለውን ያድርጉ፦**

- **የማሞግራም ቀጠሮዎን በኦንላይን ይያዙ።**



# የማኅጸን በር ካንሰርን ቀደም ብሎ ማግኘት

ለሂውማን ፓፒሎማ ቫይረስ (HPV) መከተብ እና መደበኛ የማህፀን በር የማጣሪያ ምርመራ ማድረግ የማኅጸን በር ካንሰርን ሊያስቆም ይችላል።

ከ25-74 አመት የሆናቸው ሴቶች እና የማህፀን ጫፍ ያላቸው ሰዎች በየአምስት አመቱ በህክምና ክሊኒክ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ምርመራውን እራስዎ ለማድረግ መምረጥ ይችላሉ (ናሙና በራስ መውሰድ)፣ ወይም ዶክተር ወይም ነርስ ምርመራውን ሊያደርጉልዎ ይችላሉ።

### የካንሰር ካውንስል ኤስኤ (SA) የሚከተለውን ይመክርዎታል፦

- ጸረ HPV በሽታ ክትባት መከተብ። ክትባቱ ከ12-25 አመት ለሆኑ ሰዎች ነፃ ነው። ክትባቱን በፋርማሲ ወይም በህክምና ክሊኒክ ይውሰዱ። በ 7 ኛ አመት (ክፍል) ውስጥ ያሉ ህፃናት ክትባቱን በትምህርት ቤት ይሰጣቸዋል።
- ከ25 አመት ጀምሮ የማህፀን በር የማጣሪያ ምርመራ ማድረግ።
- ቀጠሮ ሲይዙ፣ ካስፈልግዎት አስተርጓሚ ይጠይቁ። ምርጫዎ ከሆነ ሴት ሐኪም ወይም ነርስ መጠየቅ ይችላሉ።
- የማኅጸን በር ነቀርሳ ምልክቶች ካሉብዎ ሐኪምዎን ማየት። ምልክቶቹ በወር አበባዎ መካከል የደም መፍሰስ ወይም በወሲብ ወቅት ህመም መሰማትን ያካትታሉ።

**ስለ የማኅጸን ጫፍ ማጣሪያ ምርመራ፣ በራስ ናሙና የመውሰድ ምርጫን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ።**